MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

2023



የወላጅ ተከታታይ መረጃ

በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፡-

# የወላጅ መብቶች እና የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ



# መግቢያ

**የ Maryland የወላጅ መብቶች እና የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ የ Maryland ከሶስት እስከ ሃያ አንድ የወላጅ ተከታታይ መረጃ ክፍል ሲሆን፣** በሜሪላንድ ውስጥ ባሉ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቶች እና የአገልግሎት ስርዓት በመላው ስቴቱ ያሉ ቤተሰቦችን ለመደገፍ የተነደፈ የሕትመት ስብስብ ነው።



# የማውጫ ሰንጠረዥ


ገጽ 4

**የወላጅ መብቶች እና የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ**

ገጽ 4

**ሕጉ ምን ይላል**

ገጽ 5

**የእርስዎን መብቶች መረዳት**

ገጽ 8

**ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር**

ገጽ 10

**ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**


ለበለጠ መረጃ በዚህ ይጎብኙን

**www.marylandpublicschools.org**

# የ Maryland የወላጅ መብቶች
# **እና የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ**

**በ Maryland ውስጥ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁነት ሪፈር የተደረገ እያንዳንዱ ልጅ ቤተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የስቴቱን መደበኛ የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት ቅጂ ይቀበላል።**

መደበኛው የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት በፌዴራል የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ (IDEA) እና በ Maryland የተብራሩ ደንቦች ኮድ (COMAR) የተቋቋሙ የወላጅ መብቶችን ሙሉ ማብራሪያ ያካትታል።

የወላጅ መብቶች እና የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት አካል በመሆን ቤተሰቦች ስለሥርዓታዊ ከለላዎቻቸው መረጃ ለማግኘት ለማን እና የት እንደሚደውሉ መረጃ ይሰጣቸዋል።

ሁሉም የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) እና የህዝብ ኤጀንሲዎች (PA) ወላጆች መብቶቻቸውን እንዲረዱ እና በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ለመርዳት የቤተሰብ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሏቸው።

ቤተሰቦች የወላጅ መብቶቻቸውን፡ የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት ልጃቸው ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ሪፈር ሲደረግ፣ ቢያንስ በየዓመቱ፣ የጽሑፍ የስቴት ቅሬታ ወይም ተገቢ የሥነ-ሥርዓት ቅሬታ ሲደርሳቸው፣ IEP* ያለው ተማሪ እንዲታገድ ውሳኔ ሲሰጥ እና ወላጅ ጥያቄ ሲያቀርብ ማግኘት አለባቸው።

# ሕጉ ምን **ይላል**

**የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) በመላው አገሪቱ ውስጥ ላሉ የአካል ጉዳተኛ ልጆች አገልግሎቶችን የሚያረጋግጥ የፌደራል ህግ ነው።** ዓላማው ሁሉም አካል ጉዳተኛ ልጆች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የተነደፉ የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች አጽንዖት የሚሰጥ እና ለቀጣይ ትምህርት፣ ሥራ እና የግል ኑሮ የሚያዘጋጃቸው ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

# **የእርስዎን መብቶች** መረዳት

## በሜሪላንድ ውስጥ፤ ቤተሰቦች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡

### በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መረጃ ማግኘት

የ Maryland ህግ የአንድ ተማሪ IEP ወደ ቤተሰቡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲተረጎም ይጠይቃል፤ ይህም ቋንቋው በትምህርት ቤቱ ስርዓት ውስጥ ከአንድ በመቶ በላይ በሚሆን ተናጋሪ የሚነገር ከሆነ ነው። የወላጅ መብቶች የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት በሃያ አምስት የተለያዩ ቋንቋዎች የሚገኝ ሲሆን በMP4 እና በዩቲዩብ በኩል ለሚሰሙ ቤተሰቦች ተደራሽ ነው። የወላጅ መብቶች የ Maryland የሥርዓት ከለላዎች ቡክሌት ማየት ለተሳናቸው ቤተሰቦችም በጥያቄ ይገኛል።

### የ IEP ቡድን ስለልጃቸው የትምህርት ፕሮግራም የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በተመለከተ ከመተግበራቸው በፊት ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ መረጃ ማግኘት

ወላጆች ትምህርት ቤቱ በልጃቸው የትምህርት ፕሮግራም ላይ ለውጥ ከማድረጋቸው በፊት ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ማሳሰቢያ ሊደርሳቸው ይገባል፣ ይህም መለየት፣ ግምገማ፣ ምደባ፣ የተተገበሩ ግቦች፣ ማመቻቸቶች ወይም ልጃቸው የሚያገኛቸውን አገልግሎቶች ይጨምራል።

### የልጃቸውና የቤተሰባቸው የግል መረጃ ሚስጥራዊ ሆኖ እንዲቀመጥ መጠየቅ

ቤተሰቦች የልጃቸውን የትምህርት መዝገብ የመገምገም እና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንደያዘ ከተሰማቸው እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት አላቸው። ሁሉም LEAs እና PAs የተማሪ መዝገቦችን ስለማሻሻል ቤተሰቦች መከተል ያለባቸው ፖሊሲ እና አሰራሮች ሊኖራቸው ይገባል።

በጣም ጥቂት በሆኑ አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር ስለ ልጃቸው በግል የሚለይ ማንኛውም መረጃ ከመለቀቁ በፊት የወላጅ ስምምነት ያስፈልጋል። ስለ አንድ ልጅ የሚገልጽ እያንዳንዱ ሰነድ የትምህርት መዝገቡ አካል እንደሆነ ተደርጎ አይቆጠርም፣ ነገር ግን መረጃው አሁንም በሚስጥር መቀመጥ አለበት እና ከጥቂት ልዩ ሁኔታዎች በስተቀር ከወላጅ ስምምነት ውጭ ሊለቀቅ አይችልም። የአንድ ልጅ የትምህርት ሪከርድ ከት/ቤት ከወጣ በኋላ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ይደመሰሳል፣ሆኖም ግን አንድ ወላጅ እስኪደመሰስ ድረስ ከትምህርት መዝገባቸው ሰነዶችን መጠየቅ ይችላሉ። ተማሪው በተማረበት እና በሚማርባቸው የህዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል የተማሪን መዛግብት ማስተላለፍ የወላጅ ስምምነት አያስፈልገውም እናም በፍጥነት መጠናቀቅ አለበት። በሕዝብ እና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል መዝገቦችን ማስተላለፍ የወላጅ ስምምነት ያስፈልገዋል።



## የትምህርት ቤታቸው ስርዓት ለገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEE) እንዲከፍል መጠየቅ።

አንድ ቤተሰብ በ LEA ወይም PA በተጠናቀቀው ግምገማ ወይም ምዘና ውጤት የማይስማማ ከሆነ፣ ልጃቸው በትምህርት ቤቱ ሥርዓት ወይም ኤጀንሲ ተቀጥሮ በማይሠራ ገለልተኛ ገምጋሚ እንዲገመገም እና LEA ወይም PA ለምዘናው የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ የመጠየቅ መብት አላቸው። በተጨማሪም ቤተሰቡ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ግምገማ ሪፈራል ካደረጉ እና ከተማሪው IEP ቡድን በተወሰኑ የጊዜ ገደቦች ውስጥ ምንም አይነት ምላሽ ከሌለ ቤተሰቡ IEE መጠየቅ ይችላል። አንድ ቤተሰብ የ IEE ጥያቄ ሲጠይቅ፣ LEA ወይም PA በ 30 ቀናት ውስጥ ለግምገማው የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ በመስማማት ወይም ግምገማቸውን ለመከላከል መደበኛ የክርክር መፍትሄን በመጠየቅ ምላሽ መስጠት አለበት።

## ልጆቻቸው የዲሲፕሊን ጥበቃ እንደሚኖራቸው መጠበቅ።

LEA ወይም PA የተወሰኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ከወሰዱ፣ IEP ላላቸው ተማሪዎች IDEA በጣም የተወሰኑ እና ዝርዝር ሂደቶችን እና ጥበቃዎችን ይሰጣል። እነዚህ ጥበቃዎች የሚተገበሩት ለአገልግሎቶች ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች፣ ብቁነትን ለመወሰን በሂደት ውስጥ ላሉ ተማሪዎች እና ብቁ ላልሆኑ ነገር ግን LEA ወይም PA ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ መሆናቸውን ማወቅ በነበረባቸው ላይ ነው።

## ለልጃቸው የልዩ ፍላጎት የትምህርት ውሳኔ የማድረግ መብትን ይዞ መቆየት።

በ Maryland፣ ልጃቸው 18 ዓመት ሲሞላው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ውሳኔ የማድረግ መብት ከወላጆች ጋር ይቆያል። የልዩ ፍላጎት ትምህርት ውሳኔ የማድረግ መብቶች ለተማሪው ሊተላለፉ የሚችሉባቸው ውስን ሁኔታዎች አሉ። ይህ የሚከናወንበት ሂደት አለ እንዲሁም በአዋቂነት ዕድሜ ላይ ውሳኔ የማድረግ መብቶች ከመተላለፋቸው በፊት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች አሉ።

## በተናጠል ልጃቸውን በግል ትምህርት ቤት እንዲማር ማድረግ፣ ነገር ግን የትምህርት ቤቱ ስርዓት ወዲያውኑ ለትምህርቱ ገንዘብ ይሰጣል ብሎ መጠበቅ የለባቸውም።

ቤተሰቦች በ IEP ቡድን በተሰጠው ምደባ ካልተስማሙ ልጃቸውን በግል ትምህርት ቤት ሊያስገቡ ይችላሉ፣ነገር ግን LEA ወይም PA ለዚህ ምደባ ይከፍላሉ ብለው መገመት አይችሉም። ቤተሰቦች በልጃቸው ምደባ ላይ ያላቸውን ስጋት ለመፍታት እንደ ሽምግልና እና/ወይም የፍትህ ሂደት ችሎት ያሉ አለመግባባቶችን መፍቻ ሂደቶች ማግኘት ይችላሉ።

## ወላጅ ከሌለ ምትክ እንዲሾም ማድረግ

አንድ ተማሪ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደትን ለመደገፍ የወላጅ ፍቺን የሚያሟላ ግለሰብ ከሌለው፣ LEA ወይም PA ለተማሪው እንደ ወላጅ ሆኖ የሚያገለግል ምትክ ወላጅ ሊሾም ይችላል። ተተኪው ወላጅ "ስቴቱ" ሊሆን አይችልም፣ ይህም ማለት ለተማሪው የተመደበው ማህበራዊ ሰራተኛ እንደ ምትክ ወላጅ ሆኖ ሊሾም አይችልም ማለት ነው። ተተኪ ወላጅ በ LEA ወይም PA የሚሰለጥን ሲሆን፣ MSDE ስለሹመታቸው እንዲያውቅ ይደረጋል።



## ለብዙ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቶች ስምምነት መስጠት ወይም ስምምነትን መሰረዝ።

ለብዙ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቶች ስምምነት መስጠት ወይም ስምምነትን መሰረዝ።

ለሚከተሉት የወላጅ ስምምነት ያስፈልጋል፦

- ግለሰባዊ ግምገማዎችን ለማካሄድ
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን ለማስጀመር
- በተለዋጭ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ውስጥ ለመሳተፍ
- በተለዋጭ የስቴት ምዘናዎች ላይ ለመሳተፍ
- በልጃቸው IEP ወይም የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ላይ የእገዳ ወይም የማግለል አጠቃቀምን ለማካተት።

ከእነዚህ እርምጃዎች ውስጥ ለማንኛቸውም ቀደም ሲል የተሰጠ ስምምነት በቤተሰብ በማንኛውም ጊዜ ሊሻር ይችላል።

## ስለ ልጅዎ መለያ፣ ግምገማ፣ የትምህርት ምደባ ወይም ነፃ፣ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት አቅርቦትን በተመለከተ አለመግባባቶችን መፍታት።

አንዳንድ ጊዜ አጋሮች ለአንድ ልጅ በሚቀርቡ አገልግሎቶች ላይ ላይስማሙ ይችላሉ። አለመግባባቶች ከተከሰቱ ቤተሰቦች ከሚከተሉት ሂደቶች አንዱን (ወይም ሁሉንም) የመጠየቅ መብት አላቸው፡ ሽምግልና፣ የፍትህ ሂደት ችሎት፣ መደበኛ የስቴት ቅሬታ።

## ሽምግልና፡

ሽምግልና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል ሚስጥራዊና በፈቃደኝነት የሚካሄድ ሂደት ነው። የሰለጠነ አስታራቂ አጋሮቹ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እና ስለጉዳዩ አንዳቸው የሌላውን አቋም እንዲረዱ ይረዳቸዋል። የአስታራቂው ሚና አጋሮቹ በጉዳዩ ላይ እንዲወያዩ እና መፍትሄ እንዲያገኙ ማገዝ ነው። አስታራቂው አንድን ጉዳይ በተመለከተ አቋም አይይዝም፣ አንድን ወገን አይደግፍም ወይም መፍትሔ የሚሆን ሐሳብ አያቀርብም።

## የፍትህ ሂደት ችሎት፡

የፍትህ ሂደት ችሎት በአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ የሚካሄድ መደበኛ ሂደት ነው። ተከራካሪዎቹ የምስክርነት ቃላቸውን ያቀርባሉ እንዲሁም አቋማቸውን የሚደግፉ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን ያቀርባሉ። የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ ተግባር ችሎት ማካሄድ እና አለመግባባቱን የሚፈታ ውሳኔ መስጠት ነው።

## መደበኛ የስቴት ቅሬታ፡

የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ህግ (IDEA) ወይም የ Maryland ስቴት ህግ ወይም መመሪያዎችን በተመለከተ ወላጅ ጥሰት እንደተፈጸመ ካመነ የስቴት ቅሬታ ለ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ሊቀርብ ይችላል። የስቴት ቅሬታ በሚቀርብበት ጊዜ፣ MSDE ቅሬታውን የመመርመር እና ማናቸውንም ጥሰቶች ለማስተካከል (አስፈላጊ ከሆነ) ለውጦችን የመጠየቅ ሃላፊነት አለበት።



# ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች “አዎ” ብለው መመለስ ይችላሉ?

ቤተሰቦች በልጃቸው ትምህርት ውስጥ ለመሳተፍ የ Maryland የሥርዓት ከለላዎችን አሰራር መረዳታቸው አስፈላጊ ነው። ከታች ካሉት ጥያቄዎች ለአንዱ “አዎ” ብለው መመለስ ካልቻሉ፤ የአካባቢዎ ወይም የ MSDE የቤተሰብ ድጋፍ ቡድን መረጃ እና እርዳታ ሊሰጥዎት ይችላል።

### የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት

- ❍ የ Maryland ን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት—አገልግሎቶችን፣ ሂደቶችን፣ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና የሥርዓት ከለላዎችን ጨምሮ ተረድቻለሁ?
- ❍ የግምገማ ሂደቱን እና ብቁነት እንዴት እንደሚወሰን ተረድቻለሁ?
- ❍ በግምገማው ሂደት ውስጥ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ የልጄን ግምገማ በማቀድ ወቅት ስጋቶቼን እና ቅድሚያ የምሰጣቸውን ነገሮች ማካፈል እንደምችል አውቃለሁ?
- ❍ አገልግሎቱ እንዲጀመር የጽሑፍ ስምምነት ማቅረብ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ?
- ❍ ስምምነቴን ለሚጠይቅ ለማንኛውም ሂደት ስምምነቴን በማንኛውም ጊዜ መሻር እንደምችል ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ ለምን ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ እንደሆነ ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፤ ለምን እንደሆነ ተረድቻለሁ?
- ❍ የሥርዓት ከለላዎችን ለመረዳት እገዛ ካስፈለገኝ ማንን እንደማነጋግር አውቃለሁ?

### የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ-ግብር (IEP)

- ❍ የ IEP ውን ዓላማ ተረድቻለሁ?
- ❍ በ IEP ቡድን ውስጥ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ IEPን ለማጠናቀቅ እና ለመገምገም የተቀመጡ የጊዜ ሰሌዳዎችን አውቃለሁ? በማንኛውም ጊዜ የ IEP ክለሳ መጠየቅ እንደምችል ተረድቻለሁ?
- ❍ የልጄን የ IEP ግቦች እና አላማዎች፤ እንዲሁም ግቦቹን ለማሳካት ጥቅም ላይ የሚውሉትን ስልቶች እና አገልግሎቶች ተረድቻለሁ?



❍ ግቦቹ ልጄ ትምህርት ከጨረሰ በኋላ ለሽግግር እንዴት እንደሚረዱት ተረድቻለሁ?

❍ አገልግሎቶቹ መቼ እንደሚጀመሩ፣ በየምን ያህል ጊዜ እና የት እንደሚሰጡ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ አውቃለሁ?

❍ አገልግሎቱ እንዲጀመር የጽሑፍ ስምምነት ማቅረብ እንዳለብኝ ተረድቻለሁን?

❍ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ አንድ ጊዜ የጽሁፍ ፈቃድ ከሰጠሁ በኋላ፤ ደግሜ ፈቃድ መስጠት እንደማያስፈልግ አውቃለሁ?

❍ መሻሻል እንዴት እንደሚወሰን አውቃለሁ?

❍ በአገልግሎቶች ላይ ለውጦችን እንዴት እንደምጠይቅ አውቃለሁ?

❍ አገልግሎቶቹ ልጄ በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን እንዴት እንደሚረዱት ተረድቻለሁ?

❍ የሽግግሩን ሂደት– ሌሎች ኤጀንሲዎችን፣ የሽግግር እንቅስቃሴዎችን፣ ግቦችን ጨምሮ የልጄ የትምህርት መርሃ-ግብር ለእነዚህ አገልግሎቶች እንዴት እንደተዘጋጀ ተረድቻለሁ?

❍ ከትምህርት ቤት የመውጣት ሂደት ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ?

## የወላጅ ተሳትፎ፦ በ IEP ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ

❍ በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ወይም እንደ የምልክት ቋንቋ ባሉ የመግባቢያ ዘዴዎች የሚጋራ መረጃ ካስፈለገኝ፤ የአካባቢው የ IEP ቡድን ፍላጎቴን አሟልቷል?

❍ ልጄን ከትምህርት ቤቱ ጋር በመተባበር እንዴማር እንዴት እንደምረዳው ተረድቻለሁ?

❍ ስለ ልጄ የትምህርት መርሃ-ግብር ስጋት ካለብኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ?

❍ ስለ ተሟጋችነትና የቤተሰብ ድጋፍ መርሃ-ግብሮች እና እንዴት እነሱን ማግኘት እንደሚቻል አውቃለሁ?

❍ ትምህርታዊ መረጃ እንዴት እንደሚጋራ እና የልጄ መዝገብ እንዴት በምስጢር እንደሚያዝ አውቃለሁ?

❍ ለልጄ የትምህርት መርሃ-ግብር ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶችን እና ማስታወሻዎችን አስቀምጣለሁ? የሚከተሉትን የሚያካትቱ ሰነዶች፦

- ወቅታዊ እና ያለፉ IEPዎች
- የሕክምና ግምገማ ሪፖርቶች
- የግምገማ ሪፖርቶች
- የወላጅ መብቶች/የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ
- ተፈርመው የተሰራጩ የመረጃ ቅጾች
- የመምህራን ማስታወሻዎች
- ከአገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች
- ከ IEP ቡድን ስብሰባዎች የተገኙ ማስታወሻዎች
- በስልክ የተደረጉ ውይይቶች ማስታወሻዎች

❍ Maryland ስቴት አቀፍ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች (FSS) አስተባባሪዎች ትስስር እንዳለው አውቃለሁ? የ FSS አስተባባሪዎች የአካል ጉዳተኛ ልጆች ቤተሰቦችን በሚከተሉት ያግዛሉ፦

- ስለ ቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ጥያቄዎችን መመለስ
- ቤተሰቦች ለሽግግር እቅድ እንዲዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ
- አለመግባባቶችን ስለ መፍታት የበለጠ መረጃ መስጠት

❍ የጉዳይ አስተዳዳሪዬ - ለአከባቢዬ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች - አስተባባሪ መረጃን ጨምሮ የግንኙነት መረጃን ማቅረብ እንደሚችል አውቃለሁን?

# ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም **እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**

## አካባቢያዊ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አስተባባሪዎች

| የአካባቢ ትምህርት ቤት ስርዓት | ዕድሜ ከልደት እስከ 5 ዓመት | ዕድሜ ከ 5 እስከ 21 ዓመት |
|---|---|---|
| **Allegany** | 240-920-6829 | 240-920-6829 |
| **Anne Arundel** | 410-424-3270 | 410-424-3258 |
| **Baltimore City** | 410-396-1666 | 443-642-3848 |
| **Baltimore County** | 443-809-9696 | 443-809-5443 |
| **Calvert** | 443-550-8406 | 443-550-8375 |
| **Caroline** | 410-479-3609 | 410-479-3609 |
| **Carroll** | 410-751-3955 | 410-751-3955 |
| **Cecil** | 410-996-6230 | 410-996-6230 |
| **Charles** | 301-934-7456 | 301-934-7456 |
| **Dorchester** | 410-901-6915 | 410-901-6915 |
| **Frederick** | 240-578-1244 | 240-236-8744 |
| **Garrett** | 301-914-1351 | 301-914-1351 |
| **Harford** | 410-273-5579 | 410-273-5579 |
| **Howard** | 410-313-7161 | 410-313-7161 |
| **Kent** | 410-778-5708 | 410-778-5708 |
| **Montgomery** | 240-777-4809 | 240-753-9487 |
| **Prince George's** | 240-521-5054 | 301-431-5675 |
| **Queen Anne's** | 410-758-2403, x135 | 410-758-2403, x135 |
| **Somerset** | 410-651-1616, x11385 | 410-651-1616, x11385 |
| **St. Mary's** | 301-475-5511, x32218 | 240-309-4113 |
| **Talbot** | 410-822-0330 | 410-822-0330 |
| **Washington** | 301-766-8221 | 301-766-8221 |
| **Wicomico** | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| **Worcester** | 410-632-5234 | 410-632-5234 |
| **የ Maryland አይነ ስውራን ትምህርት ቤት** | 410-444-5000, x1489 | |
| **የሜሪላንድ መስማት የተሳናቸው ትም ህርት ቤት** | 443-277-8899 | |
| **የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ** | 410-767-0255 | |

**የ MARYLAND ስቴት የትምህርት መምሪያ**

**Mohammed Choudhury**
የስቴቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

**Dr. Deann Collins**
የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
የ Maryland ስቴት የትምህርት ቦርድ፣ ፕሬዝዳንት

**Wes Moore**
አስተዳዳሪ

© 2023 የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ
ይህ ህትመት የተዘጋጀው በ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ፤ የገንዘብ ድጋፍ #H393A090124A፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ለህፃናት እና ቤተሰቦች “የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎች” በ PL 105-17/111-5 መሰረት የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ/የአሜሪካ ማገገሚያ እና መልሶ ማልማት ህግ በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ነው። የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድሚያ ጣልቃገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለ Maryland ሕፃናት እና ታዳጊዎች መርሃ-ግብር መሪ ወኪል ድርጅት ነው፤ በስቴት እና በአካባቢ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች የተቀናጁ የስቴት አቀፍ የአገልግሎት መርሃ-ግብሮች እና ድጋፎች። በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ የሚያባዙ ወይም የሚያጋሩ ተጠቃሚዎች ለ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል እውቅና መስጠት አለባቸው፣ Dr. Deann Collins፤ የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ።



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

410-767-0100

www.marylandpublicschools.org

200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595